# በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ ዕቃ የሚቀመጥበትን እና የሚቆይበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## መግቢያ

አገሪቷ ላለፉት አሥር ተከታታይ ዓመታት እያስመዘገበች ባለዉ ፈጣን ዕድገት፣በተፈጠረው የኢኮኖሚ መነቃቃት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ወደ ዉጭ የሚላኩ ዕቃዎች መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ ይኽም ዕድገት ወደ ፊት በእጥፍ እንደሚያድግ ይገመታል፡፡

በአንፃሩ ዕቃን ከባሕር ወደብ የማንሳት አቅማችን በዚያው መጠን ባለማደጉ እና ከአስመጪው ጀምሮ በሂደቱ ተዋናይ በሆኑ አካላት ላይ ከሚታዩ ድክመቶችና ችግሮች፣ የማጓጓዝ ሥርዓቱ ፈጣን አለመሆኑ ፣በአገር ዉስጥ በቂ የማከማቻ መጋዘን አለመኖሩ፤ የገቢ ንግድ ዕቃዎቻችን በዉጭ ምንዛሪ ለሚከፈል ከፍተኛ የመጋዘን ኪራይ እና ዲመሬጅ /Demurrage/ እንዲሁም ከቆይታ ብዛት ለብልሽት ከመጋለጣቸዉም በላይ ለባሕር ወደብ መጨናነቅ፣ አስመጪዎች ዕቃቸውን በወቅቱ በዉላቸዉ መሠረት ማንሳት ባለመቻላቸው እና ዕቃዎች በተገቢ ጊዜ አገር ዉስጥ ባለመግባታቸዉ ሳቢያ በአገር ውስጥ የዕቃዎች እጥረት መከሰት፤ በዕቃ እጥረቱ ምክንያት የሚፈጠር የዋጋ ዉድነት፣የፋብሪካ ምርቶች መቋረጥ፣የግንባታዎች መዘግየት እንዲሁም ለልዩ ልዩ አላስፈላጊ ወጪዎችና መሰል ጉዳቶች እንዲከሰቱ ምክንያት ከመሆን በዘለለ ዕቃዎች በባህር ወደብ ላይ ከ6 ወር በላይ በመቆየታቸው በወደብ ባለቤት አገር ተወርሰው በጨረታ የመሸጥ ሁኔታ የሚደጋገም ክስተት የነበረ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ከላይ ለተጠቀሱትን ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ለመሥጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው አካላት እስካሁን ተግባራዊ ሲያደርጉት የቆዩት ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ለመወሰን በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) መሠረት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ ረቂቅ መመሪያ ተዘገጅቷል፡፡

ይህ የአሠራር ሥርዓት ሥራ ላይ የሚውለው፣ ከኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በተጨማሪ የሌሎች የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን ተግባር እና ኃላፊነት የሚሰጥ በመሆኑ በተቋቋሙበት አዋጅ በተሰጣቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት ልክ ተግባር እና

ኃላፊነት ለመወሰን እንዲቻል እንዲሁም ሥርዓቱ ከመልቲ ሞዳል አዋጅ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ የመልቲ ሞዳል አዋጅ ቁጥር 548/1999፣ የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 549/1999፣ የገቢዎችና ጉምሩክ አዋጅ 622/2001፣ የደረቅ ወደብ ለባለዕቃዉ ስለሚኖረዉ ኃላፊነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 588/2002፣ በባንክ በመያዣነት ስለተያዙ የማይንቀሳቀሱ እና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች የወጣ አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና ማሻሻያዎቹ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ የገቢ እቃዎችን የትራንዚት ጊዜ እና ወጪ ኢኮኖሚያዊነት ለማረጋገጥ ወደ ደረቅ ወደብ ተርሚናል የሚገቡ ዕቃዎችን በተቻለ ፍጥነት እየወጡ ለሌሎች ተተኪ ገቢ ዕቃዎች ቦታ እንዲለቁ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችና ደንቦችን በማይቃረን ሁኔታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ ዕቃ የሚቀመጥበትን እና የሚቆይበትን ሁኔታ ለመወሰን›› የወጣ መመሪያ ቁጥር 320/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 **‘ድርጅት’** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ነው፤

2.2 **‘የደረቅ ወደብ ተርሚናል’** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ የሌሎች ተቆጣጣሪ ተቋማት ቢሮዎችን እንዲሁም ድርጅቱ በራሱ ወጪ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ገንብቶ ወይም ተከራይቶ ገቢና ወጪ ዕቃዎችን የሚያስተናግድበት ስፍራ ነው፤

2.3 **‘የኮንቴይነር ዕቃ’** ማለት በኮንቴይነር ውስጥ የሚገኝ ንብረት ማለት ነው፤

2.4 **'የብሬክ በልክ ዕቃ'** ማለት ኮንቴይነርንና ሮሮን ሳይጨምር በሳጥን ፣ በካርቶን በጆንያና በሌላ መጠቅለያ ተጠቅልሎ የሚገኝ ወይም ከኮንቴይነር የወጣ ማናቸውም ዓይነት ንብረት ነው፤

2.5 **"የተተወ ዕቃ"** ማለት የጉምሩክን ሥነ-ሥርዓት ሳይፈጽም ለሁለት ወር ወይም የጉምሩክን ሥነ-ሥርዓት ከተፈጸመበት በኃላ ከሰባት ቀን በላይ በደረቅ ወደብና ተርሚናል ወይም በጉምሩክ መጋዘን የቆየ ዕቃ ነዉ፤

2.6 **'እፎይታ ጊዜ'** ማለት አንድ ዕቃ የደረቅ ወደብ ከደረሰ በኃላ ለ8 ቀናት ያለክፍያ በደረቅ ወደብ የሚቆይበት ጊዜ ማለት ነዉ፤

2.7 **"አዋጅ"** ማለት የማሪታይም አስተዳደር ዘርፍ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 549/1999 ነዉ፣

2.8 **ሚኒስቴር** ወይም **ሚኒስትር** ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2.9 **"ባለሥልጣን"** ማለት የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፡፡

2.10 **"ሮሮ"** ማለት በራሳቸው ጉልበት የሚጫኑ እንደ መኪና የመሳሰሉትን ጭነቶች ማለት ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ተጓጉዘው በደረቅ ወደብ ተርሚናል የገቡ ዕቃዎችን በአስመጪዎች በፍጥነት እንዲነሱለተፈለገው ዓላማ እንዲደርሱ ለማድረግ እንዲሁም በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ በገቡ ዕቃዎች ክምችት ምክንያት የሚፈጠርን መጣበብ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ነው፡፡

## 4. አስፈጻሚ አካል

በአዋጅ ቁጥር 622/2001 መሠረት የገቢዎች እና ጉሙሩክ ባለስልጣን እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 549/1999 በተደነገገው መሠረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይህንን በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ ዕቃ ስለማስቀመጥና ማቆየት የወጣውን መመሪያ የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት በጋራ ተሰጥቶአቸዋል፡፡

## 5. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ተጓጉዞ በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ በሚገኝ የግለሰብ፣ የግል ድርጅት፣ የመንግስት መስሪያ ቤትና የመንግስት የልማት ድርጅት ዕቃ ወይም በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት በተጓጓዘ እና መዳረሻዉን በደረቅ ወደብ ተርሚናል በአደረገ በማንኛዉም ዕቃ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

## 6. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ኃላፊነትና ተግባር

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ባለስልጣኑ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

6.1 የደረቅ ወደብ ተርሚናል የአገልግሎት አሠጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል እንደዚሁም ስታንዳርዱን ያሻሽላል፤

6.2 የደረቅ ወደብ ተርሚናል ታሪፍ ይቆጣጠራል፤

6.3 በደረቅ ወደብ ተርሚናል የሚሰጡ አገልግሎቶችን፣ የዕቃዎችን የቆይታ ጊዜ፣ የተወረሱ ዕቃዎችና አጠቃላይ መረጃን ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤ በኦፐሬሽን ያጋጠሙ ችግሮችን ይከታተላል፤ የመፍትሄ ኃሳብ በማካተት ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፤

6.4 የዚህን መመሪያ አተገባበር በመከታተል በአፈጻጸም ሂደት ላይ የተከሰቱ የሕግ፣ የደንብና አሠራር ክፍተቶችን በመለየት እንዲሁም የዚህ መመሪያ አካል ከሆኑ መስሪያ ቤቶች በሪፖርት መልክ የተሰበሰበው የተለየ የሕግ፣ የደንብና የአሠራር ክፍተቶችን በመለየት የሚመለከታቸዉን አካላትን በማስተባበር ክፍተቶቹ የሚስተካከሉበትን በጥናት ላይ የተመሠረተ የመፍትሄ ኃሣብ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያቀርባል፤

6.5 በዚህ መመሪያ ተግባር እና ኃላፊነት የተሰጣቸዉ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች መመሪያዉን ለመተግበር ተግባር እና ኃላፊነታቸዉን እየተወጡ መሆኑን ይከታተላል፤ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል፤

6.6 ዕቃዎቻቸውን በወቅቱ ከደረቅ ወደብ ያላነሱ አስመጪዎችን የችግሮች ምንጭ በመለየት የሚመለከታቸዉን አካላት በማስተባበር መፍትሄ እና የዉሳኔ ኃሣብ በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

## 7 የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኃላፊነትና ተግባር

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ባለስልጣኑ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፣

7.1 በአዋጅ ቁጥር 622/2001 በተሰጠው ሥልጣንና ከድርጅቱ በሚቀርብለት በደረቅ

ወደብና ተርሚናል ሁለት ወር ያስቆጠሩ የገቢ ዕቃዎች ዝርዝር መሠረት ወደ ጉምሩክ የተተወ ዕቃ መጋዘን ያዘዋውራል፣

7.2 በደረቅ ወደበ ተርሚናል ማስቀመጫ በተተው ዕቃዎች ላይ ባለድርሻ አካላት የሆኑትን ንግድ ባንክ እና አስመጪውን ባሳተፈ መልኩ ወይም ድርጅቱ የተተወ ዕቃ በሚስወግድበት የዉስጥ አሰራሩ መሠረት የተተዉ ዕቃዎችን በማስወገድ የድርጅቱ የየብስ ወደብ ጥበት ሥጋት እንዲቀንስ ያደርጋል፤

7.3 ተደጋጋሚ ማስታወቂያ ከድርጀቱ ደርሶአቸዉ ዕቃቸዉን ከደረቅ ወደብ ላይ በ60 ቀናት ውስጥ የማያነሱ አስመጪዎችን ከድርጅቱ በሚላክለት ሪፖርት መሠረት በመለየትና በማጠናቀር በቀጣይ የዉጭ ምንዛሪ ፍቃድ እንዳያገኙ ለብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፤ እንዲሁም ከመንግሥት ማንኛዉም ድጋፍ እንዳያገኙ ዝርዝራቸዉን ለንግድ ሚኒስቴር ያሳወቃል፤

7.4 በደረቅ ወደብና ተርሚናል የተተዉ ዕቃዎች አወጋገድ በተመለከተ በተተዉ ዕቃዎች ላይ መብት ያላቸዉ ድርጅቶች መረጃ በሚጠይቁበት ወቅት አስፈላጊዉን መረጃ ይሰጣል፤

7.5 ይህን መመሪያ በማስፈጸም ሂደት የሕግ፣ የደንብና የአሠራር ክፍተቶችን በመለየት ክፍተቶቹ የሚስተካከሉበትን በጥናት ላይ የተመሠረተ የመፍትሄ ሃሣብ በማዘጋጀት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያቀርባል፡፡

## 8 የድርጅቱ ተግባርና ኃላፊነት

በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 136/1999 የደረቅ ወደብን ኃላፊነት በተመለከተ የተደነገገው መመሪያ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 588/2002 የደረቅ ወደብ ለባለዕቃዉ ስለሚኖረዉ ኃላፊነት የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ድርጅቱ የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል።

8.1 የደረቅ ወደብ ተርሚናል ዕህፈት ቤቶችን የሥራ ሰዓት ያሳውቃል፤

8.2 ለማንኛውም የዕቃ አስመጪ ወይም ዕቃ ተረካቢ በደረቅ ወደብ ተርሚናል ዕህፈት ቤት የደረሰውን ዕቃ ዕህፈት ቤቱ ለስምንት (8) ቀናት ያለክፍያ የማቆየት የወደብ አገልግሎት ይሰጣል፣

8.3 በአንቀጽ 8.2 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከችሮታ ጊዜ በላይ ለሚቆይ ዕቃ ለአስመጪዉ የተሰጠዉን አገልግሎት በድርጅቱ አሠራር እና ታሪፍ መሠረት ዕቃዉን ለማቆየት የተሰጠዉን የአገልግሎት ክፍያ ከአስመጪዉ ላይ ይሰበስባል፤ እንዲሁም አሠራሩን እና ታሪፉን ለባለሥጣን መ/ቤቱ ያሳዉቃል፤

8.4 የዕቃ አስመጪውን ማንነት እና አድራሻውን የሚገልፅ የተሟላ መረጃ ይይዛል፤

8.5 ዕቃው የደረቅ ወደብ ተርሚናል ከደረሰ በኂላ ለዕቃ አስመጪው በስልክ ወይም በደብዳቤ ወይም በፋክስ ወይም በኢ-ሜይል ወይም በራሱ ድረ-ገጽ ወይም በጋዜጣ ወይም በድርጅቱ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በማውጣት ያሳውቃል፤

8.6 ዕቃው በኮንቴይነር ውስጥ ያለ ወይም ብሬክ በልክ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8.4 መሠረት ለዕቃ አስመጪው የሚላከው መልዕክት የሚከተለውን ማካተት አለበት፡-

- ሀ. የአሰመጪውን ሙሉ ስም፤
- ለ. የቢል ኦፍ ሎዲንግ ቁጥር፤
- ሐ. ዕቃው በኮንቴይነር ውስጥ ያለ ወይም ብሬክ በልክ መሆኑን እና መለያ ቁጥሩን፣
- መ. ዕቃው የደረቅ ወደብ ተርሚናል የደረሰበትን ቀንና የቆየበት ጊዜ፤ እንዲሁም
- ሠ. የኮንቴይነሩ መጠን፤

8.7 ዕቃው ተሽከርካሪ ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.5 መሠረት ለዕቃው አስመጪው የሚላከው መልዕክት የሚከተለውን ማካተት አለበት፡-

ሀ. የአስመጪውን ሙሉ ስም፤

ለ. የቢል ኦፍ ሎዲንግ ቁጥር፤

ሐ. የተሽከርካሪው ዓይነት መግለጫ፤

መ. በኮንቴይነር የመጣ ከሆነ የኮንቴይነር ቁጥር፤

ሠ. የተሽከርካሪውን ሞተርና ሻሲ ቁጥር፤ እና

ረ. ዕቃው የደረቅ ወደብ ተርሚናል ዕህፈት ቤት የደረሰበትን ቀንና የቆየበትን ጊዜ፡፡

8.8 ዕቃ አስመጪው ወይም ዕቃ ተረካቢው ዕቃው የደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ በገባ በተሠጠው የ 8(ስምንት) ቀናት የችሮታ ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ካላወጣ ዕቃ አስመጪው ወይም ዕቃ ተረካቢው ዕቃውን እንዲያወጣ ድርጅቱ የመጀመሪያ ማስታወቂያ ለዕቃ አአስመጪው ወይም ለዕቃ ተረካቢው በንዑስ አንቀጽ 8.5 በተገለጹት አማራጮች ይልካል፤

8.9 ዕቃ አስመጪው ወይም ዕቃ ተረካቢው የደረቅ ወደብ ተርሚናል የሚገኘውን ዕቃውን እንዲያነሳ የመጀመሪያ ማስታወቂያ በተፃፈለት ቀጣይ 20 (ሃያ) ቀናት ውስጥ ካላወጣ ዕቃው በዕቃ አስመጪው ወጪ ወደ ሌላ ቦታ ሊዛወር የሚችል መሆኑን በመግለጽ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 8.5 በተገለጹት አማራጮች መሠራት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ድርጅቱ ለዕቃ አስመጪው ወይም ለዕቃ ተረካቢው ይሰጣል፤

8.10 በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ ከ45 (አርባ አምስት) ቀናት በላይ የቆየ ዕቃ ድርጅቱ ለቦታ አጠቃቀም እንዲመቸው ከነኮንቴይነሩ ወይም ከኮንቴይነር በማውጣት ለማዛወር ቦታ ያደራጃል፤ ለገቢዎች እና ጉሙሩክ ባለስልጣን በማሳወቅ ዕቃዎቹን ሊያዘዋዉር ይችላል፤ እንዲሁም ተገቢውን ጥበቃ ያደርጋል፤

8.11 በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ ያሉትን ከ 7 (ሰባት) ቀን በላይ የሆናቸውን ዕቃዎች፤ በደረቅ ወደብ ተርሚናል ውስጥ ከ45 (አርባ አምስት) ቀን በላይ ሆኗቸዉ ወደ ሌላ ስፍራ የተዛወሩትን፤ እንዲሁም የደረቅ ወደብ ከገቡ በድምሩ 2 (ሁለት) ወር እና ከዚያ በላይ በመቆየታቸዉ ምክንያት በጉምሩክ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ

28 መሠረት ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ዝርዝራቸዉ የተላለፈ ዕቃዎችን በመጨመር፤ የየወሩን ሪፖርት ወር በገባ በ5 (አምስት) ቀናት ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣን መ/ቤት እና ለሚመለከታቸዉ የመንግሥት አካላት ያቀርባል፤

8.12 በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8.11 ላይ የተገለጸዉን ተግባር የሚያከናዉን እንዲሁም በጉምሩክ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 28 እና ተከታዮቹ ላይ በተደነገገዉ ጊዜ ገደብ ዉስጥ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ባለመፈጸሙ እንደ ተተወ ዕቃ የሚቆጠር በደረቅ ወደብ ተርሚናል ዉስጥ የሚገኝ ማንኛዉንም ዕቃ ዝርዝር ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት የሚያሳዉቅ፤ የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት ማስወገዱን የሚከታተል፤ የማስወገዱ ተግባር በመ/ቤቱ በኩል በተገቢዉ ጊዜ እንዲከናወን የሚስታዉስ ፣ ድርጅቱ ዕቃዉን ለማጓጓዝ ያወጣዉን ወጪ በማሳወቅ በጉምሩክ የዕዳ አከፋፈል ሥርዓት መሠረት ከተተወዉ ዕቃ ሽያጭ ላይ የድርጅቱን ድርሻ የሚሰበስብ እንዲሁም የተተዉ ዕቃችን በተመለከተ አፈጻጸሙን በመከታተል ለሚመለከታቸዉ አካላት ሪፖርት የሚያቀርብ አቅም ያደራጃል /ይገነባል ፣

8.13 አደገኛ ዕቃን ከተጫነበት ተሽከርካሪ ሳይወርድ ተፈትሾ ለማስቀመጥ ወደተዘጋጀበት መዳረሻ እንዲጓጓዝ ከገቢዎችና ምሩክ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ይሠራል፤

8.14 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8.2 ላይ ከተጠቀሰዉ የእፎይታ ጊዜ በላይ ለሚዘገዩ ዕቃዎች በድርጅቱ የማስተናገድ ብቃት ማነስ ምክንያት አስመጪዉ ዕቃዉን ሳያነሳ ቢቀር አስመጪዉ ከተጨማሪ የደረቅ ወደብ የቆይታ ክፍያ ነፃ ይሆናል፤

8.15 በደረቅ ወደብና ተርሚናል ውስጥ 30 (ሰላሳ) ቀናት እና ከዚያ በላይ የቆየ ዕቃ ካለና የኮንቴነር እጥረት ከተከሰተ ድርጅቱ በዉጪ ምንዛሪ የሚከፈልን የኮንቴነር ኪራይ ለመቀነስ እንዲሁም በኮንቴነር ክምችት ብዛት ሊከሰት የሚችለዉን የየብስ ወደብ ጥበት ለማስቀረት ሲባል እንደ ዕቃዎቹ ዓይነት እና ባሕርይ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባለበት ዕቃዎቹን ከኮንቴነር ዉስጥ በማዉጣት ምቹ ነዉ ብሎ ባመነበት ቦታ ሊያስቀምጥ ይችላል፤

8.16 ድርጅቱ ዕቃውን ወደ ሌላ ስፍራ በሚያዛውርበት ጊዜ ወይም ከኮንቴይነር አውጥቶ በሚያስቀምጥበት ጊዜ ይህንን የሚመራበት የውስጥ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይችላል፤

8.17 ድርጅቱ ከኮንቴነር ዉስጥ ወጥቶም ይሁን ሳይወጣ ወደ ሌላ ቦታ የተዛወረ ዕቃን በተመለከተ የተዛወረውን ዕቃ ዓይነትና የተዛወረበትን ቦታ የሚገልፅ መረጃ መያዝ

አለበት፤ እንዲሁም የደብዳቤ፣ የፋክስ ወይም የኢ-ሜይል መልዕክት ለዕቃ አስመጪው ወይም ዕቃ ተረካቢው መላክ አለበት፤

8.18 በመመሪያዉ አንቀጽ 9.4 ላይ በተቀመጠዉ ድንጋጌ መሠረት አስመጪዉ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ለድርጅቱ በማቅረብ ዝዉዉሩ እንዲዘገይ የተፈቀደለት ዕቃ ድርጅቱ ባስቀመጠለት ጊዜ ገደብ ዉስጥ አስመጪዉ ዕቃዉን ካላነሳ እንደ ዕቃዉ ባሕሪ ከኮንቴነር ሳይወጣ ወይም በማዉጣት እንዲዘዋወር ሊያደርግ ይችላል፤

## 9. የዕቃ አስመጪው ወይም ዕቃ ተረካቢው ተግባርና ኃላፊነት፣

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የዕቃ አስመጪው ወይም ዕቃ ተረካቢው የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

9.1 ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሲከፍት ሙሉ አድራሻውን ማስመዝገበ አለበት፤

9.2 ዕቃው በደረቅ ወደብና ተርሚናል ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በተፈቀደው የእፎይታ ጊዜ ውስጥ ያወጣል፤

9.3 በደረቅ ወደብና ተርሚናል ለሚያገኘው የወደብ አገልግሎት በታሪፍ መመሪያው መሠረት ለዕቃዉ የተሰጠዉን ክፍያ የመፈፀም ግዴታ አለበት፤

9.4 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8.9 እንደተደገለጸዉ አስመጪዉ ዕቃዉን ከደረቅ ወደብ ዕቃውን እዲያነሳ በተሠጠዉ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መሠረት ዕቃዉን የማያነሳበት ከአስመጪዉ ችግር ውጪ መሆኑን የሚስረዳ በቂ ምክንያት ካለዉ ለድርጅቱ ማቅረብ ይችላል፤

9.5 ድርጅቱ ዕቃውን ከነኮንቴይነሩ ወይም ከኮንቴይነሩ አውጥቶ ለማዛወር የሚያወጣውን ተጨማሪ ወጪ አስመጪው የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

9.6 ዕቃዉ የጠፋዉ ወይም ጉዳት ደረሰበት ወይም ርክክቡ የዘገየዉ አስመጪዉ ወይም ዕቃ ተረካቢዉ ዕቃዉን እንዲያነሳ ከድርጅቱ በተሰጠዉ ማስታወቂያ መሰረት ዕቃዉን ባለማንሳቱ ምክንያት በማስረከቢያዉ ቦታ ተፈጻሚ በሚሆነዉ ልዩ አሰራር ወይም ህግ በመፈጸሙ ከሆነ በዕቃዉ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት የደረቅ ወደብ ስለባለዕቃዉ ስለሚኖረዉ ኃላፊነት ለመወሰን በወጣዉ በአዋጅ ቁጥር 588/2002 አንቀጽ 4 (3) እና በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999 አንቀጽ 15 (2) ለ/ ii ላይ በተደነገገዉ መሠረት ስለ ዕቃዉ ጉዳት ድርጅቱን መጠየቅ አይችልም፡፡

9.7 ከ30 (ሰላሳ) ቀናት በላይ በመቆየት ወደ ሌላ የተዛወሩ ዕቃዎች የመጋዘን ኪራይ በ 30ኛው ቀን ላይ ከሚከፈል ታሪፍ በተጨማሪ በየቀኑ በ 0.05% በመጨመር ይከፍላል፡፡

## 10. የብሔራዊ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት

ይህን መመሪያ በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ የሚተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

10.1 ዕቃ እያስመጡ በተገቢው ጊዜ ከደረቅ ወደብና ተርሚናል ዕቃቸውን የማያነሱ አስመጪዎች ያስመጡትን ዕቃ ካለነሱ ሌላ ዕቃ ለማስገባት እንዳይችሉ ከንግድ ባንኮችን ፈቃድ እና ድጋፍ እንዳያገኙ በአንቀጽ 10.2 እና 10.3 በተቀመጠው መሠረት ተፈጻሚ ያደርጋል፤

10.2 በአንቀጽ 9.1 ላይ የሚካተቱ አስመጪዎች ዝርዝር ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሲደርሰዉ ይህንኑ ዝርዝር ለሁሉም ንግድ ባንኮች ያስተላልፋል፡፡ አስመጪዎች ዕቃቸውን ሲያነሱ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ዝርዝሩን አሻሽሎ ሲልክ አስመጪዎቹ ፈቃድ ማግኘት እንዲችሉ ብሔራዊ ባንክ ለሁሉም ንግድ ባንኮች ያሳውቃል፡፡

10.3 ንግድ ባንኮች በተሰጣቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት መሠረት ሥራቸዉን እንዲያከናዉኑ ከላይ በአንቀጽ 10.2 በተጠቀሠው መሠረት መመሪያ ይሰጣል፤ እንዲሁም በማይተገብሩት ላይ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚደርሰዉ መረጃ መሠረት የማስተካከያ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰወዳል፡፡

## 11. የንግድ ባንክ ተግባር እና ኃላፊነት

ይህን መመሪያ በተመለከተ የንግድ ባንክ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

11.1 የአስመጪዎችን አስፈላጊ ሰነዶች (Bill of Loading) በወቅቱ መድረሳቸውን ያሳውቃል ፤

11.2 የባንክ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የአስመጪዎችን የተሟላ አድራሻ ይመዘግባል፡፡

# ክፍል ሶስት

# ልዩልዩ ድንጋጌዎች

## 12. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በደረቅ ወደብ ውስጥ 30(ሠላሳ) ቀን ለቆየ ዕቃ ድርጅቱ ለዕቃ አስመጪው ወይም ለዕቃ ተረካቢው የ20 (ሃያ) ቀን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በማስጠንቀቂያዉ ጊዜ ውስጥ አስመጪዉ ዕቃውን ካላነሳ ድርጅቱ ዕቃውን ወደ ሌላ ቦታ ሊያዛውር ይችላል በዚህ ሁኔታ በተዛወረው ዕቃ ላይም የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 13. የማስፈጸሚያ ስልት

በዚህ መመሪያ በቅጥያነት አባሪ ሆኖ የተያያዘዉ የደረቅ ወደብና ተርሚናል የአገልግሎት ስታንዳርድ የሥራዉን ሂደት እና የመመሪያዉን አፈጻጸም ለመከታተል የሚያስችል የአሰራር ስታንዳርድ የዚህ መመሪያ አካል ሆኖ ይፈጸማል፡፡

## 14. መመሪያዉን ስለ ማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህ መመሪያ ሊሻሻል ይገባዋል ብሎ በአመነ ጊዜ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊያሻሽለዉ ይችላል ፡፡

## 15. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 1 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ወርቅነህ ገበየሁ**

**የትራንስፖርት ሚኒስትር**